የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ህዳር ፳ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 4
ADDIS ABABA 29th November 2012

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፸/፪ሺ፭ ዓ.ም.
የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.... ........................................................ገጽ ፮ሺ፮፻፵፮
ሠንጠረዥ..........................................ገጽ ፮ሺ፮፻፶፫

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸/፪ሺ፭

## ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬ አንቀጽ ፴፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 12.85

CONTENTS

Regulation No. 270/2012
Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation............ ........... ................................................ Page 6646
Schedule ................................................Page 6653

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 270/2012

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION ON INVESTMENT INCENTIVES AND INVESTMENT AREAS RESERVED FOR DOMESTIC INVESTORS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 39 of the Investment Proclamation No. 769/2012.

### PART ONE

### GENERAL

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation No. 270/2012".

2. Definitions

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Investment Proclamation No. 769/2012;

2/ the definitions provided for in Article 2 of the Proclamation shall also apply to this Regulation;

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፫/ "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፱/፪ሺ፭ እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ነው፤

፬/ "ቦርድ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፱/፪ሺ፭ አንቀጽ ፮(፩) የተመለከተው የኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤

፭/ "የካፒታል ዕቃ" ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ወይም ዕቃዎች እና አክሰሰሪዎቻቸው ሲሆኑ ለእነዚሁ አገልግሎት የሚውሉ የወርክሾፕ እና የላብራቶሪ መሣሪያዎችንና ዕቃዎችን ይጨምራል፤

፮/ "የግንባታ ዕቃ" ማለት ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ግንባታ የሚያገለግሉ መሠረታዊ ግብዓቶችን ያጠቃልላል፤

፯/ "የጉምሩክ ቀረጥ" ማለት በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጣሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችንም ይጨምራል፤

፰/ "የገቢ ግብር" ማለት የፌደራሉ መንግሥት ወይም የክልል መንግሥታት ወይም የሁለቱ የጋራ ገቢ የሆነ በትርፍ ላይ የሚጣል ታክስ ነው፡፡

3/ "Agency" means the Ethiopian Investment Agency re-established under the Council of Ministers Regulation No. 269/2012;

4/ "Board" means the Investment Board referred to in Article 6(1) of the Council of Ministers Regulation No. 269/2012;

5/ "capital goods" means machinery, equipment and their accessories needed to produce goods or render services and include workshop and laboratory machinery and equipment necessary for same;

6/ "construction material" includes basic inputs necessary for the construction of investment projects;

7/ "customs duty" includes indirect taxes levied on imported goods;

8/ "income tax" means tax levied on profits from business and categorized as the revenue of the federal government, regional governments or as their joint revenue.

## ፫. ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች

፩/ የሚከተሉት የሥራ መስኮች ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባላቸው ባለሀብቶች ብቻ የሚካሄዱ ይሆናሉ፡-

ሀ) የባንክ፣ የኢንሹራንስ እና አነስተኛ የብድርና የቁጠባ ተቋም ሥራዎች፤

ለ) ዕቃዎችን የማሸግ፣ የማስተላለፍ እና የመርከብ ውክልና አገልግሎቶች፤

ሐ) የብሮድካስቲንግ አገልግሎት፤

መ) የመገናኛ ብዙኃን ሥራዎች፤

ሠ) የጥብቅና እና የሕግ ማማከር አገልግሎት፤

ረ) አገር-በቀል ባህላዊ መድኃኒቶችን ማዘጋጀት፤

ሰ) የማስታወቂያ፣ የፕሮሞሽን እና የትርጉም ሥራዎች፤

ሸ) እስከ ፶ መንገደኞች የመጫን አቅም ባለው አውሮፕላን የሚሰጥ የአገር ውስጥ የመንገደኞች የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም አንድ የንግድ ማኅበር ኢትዮጵያዊ ዜግነት አለው የሚባለው የማኅበሩ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ባለቤትነት የተያዘ እንደሆነ ነው፡፡

## 3. Investment Areas Reserved for Domestic Investors

1/ The following areas of investment are exclusively reserved for Ethiopian nationals:

a) banking, insurance and micro-credit and saving services;

b) packaging, forwarding and shipping agency services;

c) broadcasting service;

d) mass media services;

e) attorney and legal consultancy services;

f) preparation of indigenous traditional medicines;

g) advertisement, promotion and translation works;

h) air transport services using aircraft with a seating capacity up to 50 passengers.

2/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, a business organization may have Ethiopian nationality, provided that its total capital is owned by Ethiopian nationals.

**፬. ለውጭ ባለሀብቶች ስለተፈቀዱ የሥራ መስኮች**

፩/ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር ፩.፫.፫፣ ፩.፬.፪፣ ፩.፯፣ ፩.፲፩.፫፣ ፩.፲፩.፬፣ ፭.፫፣ ፮.፪፣ ፰.፪፣ ፱.፪፣ ፱.፫ እና ፲፪ ከተመለከቱት በስተቀር በሠንጠረዡ በተመለከቱት ሌሎች የሥራ መስኮች የውጭ ባለሀብት ኢንቨስት ማድረግ ይፈቀድለታል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በአዋጁ አንቀጽ ፮(፩) እና (፪) እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫(፩) ከተመለከቱት በስተቀር የውጭ ባለሀብቶች በሠንጠረዡ ከተዘረዘሩት ውጭ በሌሎች የሥራ መስኮች እንዲሳተፉ ቦርዱ ሊፈቅድ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት በኢንቨስትመንት ሥራ የተሠማራ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ለሥራው የሚያስፈልገው የግል የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለቤት ሊሆን ይችላል።

## ክፍል ሁለት
## የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች

### ንዑስ ክፍል አንድ
### የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ

**፭. ለአዲስ ድርጅት ስለሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ**

፩/ አዲስ ድርጅት ለማቋቋም ኢንቨስት የሚያደርግ ባለሀብት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናል።

፪/ አዲስ ድርጅት ለማቋቋም፡-

ሀ) በጋምቤላ ሕዝቦች ክልል፤

ለ) በቤንሻንጉል/ጉሙዝ ክልል፤

ሐ) በአፋር ክልል (ከአዋሽ ወንዝ እስከ ፲፭ ኪሎ ሜትር ግራና ቀኝ ካሉ አካባቢዎች በስተቀር)፤

መ) በሱማሌ ክልል፤

ሠ) በኦሮሚያ ክልል በጉጂና ቦረና ዞኖች፤ ወይም

ረ) በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን፣ በሰገን (ደራሼ፣ አማሮ፣ ኮንሶና ቡርጂ) አካባቢ ሕዝቦች ዞን፣ በቤንች ማጂ ዞን፣ በሸካ ዞን፣ በዳውሮ ዞን፣ በከፋ ዞን ወይም በኮንታና በባስኬቶ ልዩ ወረዳዎች፤

ኢንቨስት የሚያደርግ ባለሀብት በሠንጠረዡ በተመለከተው መሠረት የሚያገኘው የገቢ ግብር ማበረታቻ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት በየዓመቱ የ፴ በመቶ የገቢ ግብር ቅናሽ ይደረግለታል።



**4. Investment Areas Allowed for Foreign Investors**

1/ A foreign investor shall be allowed to invest in areas of investment specified in the Schedule attached hereto, except those areas provided for in number 1.3.3, 1.4.2, 1.7, 1.11.3, 1.11.4, 5.3, 6.2, 8.2, 9.2, 9.3 and 12 of the Schedule.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Board may allow foreign investors to invest in areas other than those specified in the Schedule, except those areas provided for in Article 6 (1) and (2) of the Proclamation and Article 3(1) of this Regulation.

3/ A foreign investor who invests pursuant to sub-article (1) or (2) of this Article may acquire a private commercial road transport vehicle necessary for his business operations.

## PART TWO
## INVESTMENT INCENTIVES

### SECTION ONE
### EXEMPTION FROM INCOME TAX

**5. Income Tax Exemption for New Enterprise**

1/ Any investor who invests to establish a new enterprise shall be entitled to income tax exemption as provided for in the Schedule attached hereto.

2/ Any investor who invests to establish a new enterprise in:

a) the State of Gambela Peoples;

b) the State of Benshangul/Gumuz;

c) the State of Afar (except in areas within 15 kilo meters right and left of the Awash River);

d) the State of Somali;

e) Guji and Borena Zones of the State of Oromia; or

f) South Omo Zone, Segen (Derashe, Amaro, Konso and Burji) Area Peoples Zone, Bench-Maji Zone, Sheka Zone, Dawro Zone, Kaffa Zone or Konta and Basketo Special Woredas of the State of Southern Nations, Nationalities and Peoples;

shall be entitled to an income tax deduction of 30% for three consecutive years after the expiry of the income tax exemption period specified in the Schedule attached hereto.

## ፮. ነባር ድርጅት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ስለሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ

በአዋጁ አንቀጽ ፪(፰) መሠረት ነባር ድርጅቱን ያስፋፋ ወይም ያሻሻለ ባለሀብት ከማስፋፊያው ወይም ከማሻሻያው ለሚያገኘው ተጨማሪ ገቢ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት ያገኛል፡፡

## ፯. ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት ስለሚሰጥ ተጨማሪ የገቢ ግብር ማበረታቻ

ማንኛውም ባለሀብት ቢያንስ ፷በመቶ የሚሆነውን ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ወይም በአገልግሎት ግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ በሠንጠረዡ ከተፈቀደለት በተጨማሪ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ ይሆናል፡፡

## ፰. ማበረታቻ ስለሚቀንስበት ሁኔታ

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭፣ ፮ እና ፯ የተደነገገው ቢኖርም የራሱን የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ ሕንፃ ሳይገነባ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ በተመለከቱት የማምረቻ ኢንዱስትሪ ወይም የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት የሥራ መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት የሚያገኘው የገቢ ግብር ማበረታቻ በሠንጠረዡ ለየሥራ መስኩ ከተመለከተው በአንድ ዓመት ያነሰ ይሆናል፡፡

## ፱. መረጃ ስለማቅረብ

ማንኛውም ባለሀብት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭፣ ፮ እና ፯ ለተመለከቱት የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ የሚሆነው አስፈላጊውን መረጃ አግባብ ላለው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

## ፲. ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን መቆጠር ስለሚጀምርበት ጊዜ

፩/ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው ባለሀብቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይሆናል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል ባለሀብቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት የጀመረበትን ጊዜ ለሚመለከተው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ያሳውቃል፡፡

## ፲፩. በገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን ገቢን ስለማሳወቅ

የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ባለሀብት ከገቢ ግብር ነፃ በሆነበት ዘመን የሚያገኘውን ገቢ አግባብ ላለው የገቢ ግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት በየዓመቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 6. Income Tax Exemption for Expansion or Upgrading of Existing Enterprise

Any investor expanding or upgrading his existing enterprise pursuant to Article 2(8) of the Proclamation shall, with respect to the additional income generated by the expansion or upgrading, be entitled to income tax exemption as provided for in the Schedule attached hereto.

## 7. Additional Income Tax Exemption for Investors Exporting Products or Services

Any investor who exports or supplies to an exporter as production or service input, at least 60% of his products or services shall be entitled to income tax exemption for two years in addition to the exemption provided for in the Schedule attached hereto.

## 8. Condition for Reducing Incentive

Notwithstanding the provisions of Article 5, 6 and 7 of this Regulation, the income tax exemption to be granted to an investor who engages in an area of manufacturing industry or information and communication technology development, without constructing his own production or service rendering building, shall be one year lesser than what is provided for in the Schedule attached hereto.

## 9. Duty to Submit Information

An investor shall be entitled to the exemptions specified in Article 5, 6 and 7 of this Regulation provided that he submits all the required information to the relevant tax authority.

## 10. Commencement of Period of Income Tax Exemption

1/ The period of exemption from income tax shall begin from the commencement date of production or provision of service by the investor.

2/ For the implementation of sub-article (1) of this Article, the appropriate investment organ shall notify the relevant tax collecting authority the commencement date of production or provision of service by the investor.

## 11. Declaration of Income During Income Tax Exemption Period

An investor who is entitled to income tax exemption shall declare, every year, the income he has obtained during the exemption period to the appropriate tax collecting authority.

## ፲፪. ኪሣራን ስለማስተላለፍ

፩/ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ በተሰጠበት ዘመን ውስጥ ኪሣራ ያጋጠመው ማንኛውም ባለሀብት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመኑ ከተጠናቀቀ በኋላ የዚሁ ዘመን ግማሽ ለሚሆን ጊዜ ኪሣራው ይተላለፍለታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ኪሳራን የማስተላለፍ ዘመን ሲሰላ ግማሽ ዓመት ያጋጠመ እንደሆነ እንደሙሉ የገቢ ግብር ዘመን ይቆጠራል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም በገቢ ግብር ነፃ የመሆኛ ዘመን ኪሣራ የደረሰበት ማንኛውም ባለሀብት የደረሰበትን ኪሣራ ከአምስት የገቢ ግብር ዘመን በላይ ማስተላለፍ አይችልም፡፡

### ንዑስ ክፍል ሁለት

### የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ

## ፲፫. የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለመሆን

፩/ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር ፯፣ ፲፩፣ ፲፬ እና ፲፭ የተመለከቱትን ሳይጨምር በሠንጠረዡ ከተዘረዘሩት የሥራ መስኮች በአንዱ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ለሚያቋቁመው አዲስ ድርጅት ወይም ነባር ድርጅቱን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈልጋቸውን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ለሚመለከተው የኢንቨስትመንት አካል በቅድሚያ በማቅረብ ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

፫/ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሀብት ከአገር ውስጥ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃዎችን ሲገዛ ዕቃዎቹን ለማምረት በግብዓትነት በዋሉት ጥሬ ዕቃዎች ወይም አካሎች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የሚፈቀድለት ማንኛውም ባለሀብት ዋጋቸው ከካፒታል ዕቃዎቹ ጠቅላላ ዋጋ ፲፭ በመቶ የማይበልጡ መለዋወጫዎችን ፕሮጀክቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

## ፲፬. የተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መሆን

ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡበት ሁኔታ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ዓይነትና ባህሪ መሠረት በማድረግ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 12. Loss Carry Forward

1/ An investor who has incurred loss within the period of income tax exemption shall be allowed to carry forward such loss for half of the income tax exemption period after the expiry of such period.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, for the purpose of calculating the period of loss carry forward, a half-year period shall be considered as a full income tax period.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) and (2) of this Article, an investor who has incurred loss during the income tax exemption period may not be allowed to carry forward such loss for more than five income tax period.

### SECTION TWO

### EXEMPTION FROM CUSTOMS DUTY

## 13. Exemption of Capital Goods and Construction Materials from Customs Duty

1/ Any investor engaged in one of the areas of investment specified in the Schedule attached hereto, except those specified under numbers 7, 11, 14 and 15 of the Schedule, may import duty-free capital goods and construction materials necessary for the establishment of a new enterprise or the expansion or upgrading of an existing enterprise.

2/ For the implementation of sub-article (1) of this Article, the investor shall submit, in advance, the list of capital goods and construction materials to be imported duty-free and get approval of same from the appropriate investment organ.

3/ If an investor entitled to a duty-free incentive buys capital goods or construction materials from local manufacturing industries, he shall be refunded with the customs duty paid for the raw materials or components used as inputs for the production of such goods.

4/ An investor eligible to a duty-free incentive pursuant to this Article, shall be allowed to import spare parts the value of which is not greater than 15% of the total value of the capital goods within five years from the date of commissioning of his project.

## 14. Exemption of Motor Vehicles from Customs Duties

The total or partial exemptions of motor vehicles from customs duties shall be determined by directive to be issued by the Board based on the types and nature of investment projects.

፲፭. ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ዕቃን ስለማስተላለፍ

፩/ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ማናቸውም የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃ ወይም ተሽከርካሪ ተመሳሳይ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ላለው ሰው ሊተላለፍ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም አስቀድሞ ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥ ተከፍሎ የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃው ወይም ተሽከርካሪው የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ሊተላለፍ ይችላል።

፫/ ባለሀብቱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ ያስገባውን የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃ ወይም ተሽከርካሪ መልሶ ከአገር እንዲወጣ ማድረግ ይችላል።

፬/ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ባለሀብት አግባብ ባለው የጉምሩክ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል።

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፮. ስለተሻረና ተፈጻሚነት ስለማይኖረው ሕግ

፩/ ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፬/፲፱፻፺፮ (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፪/ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፲፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ የተደነገገው ቢኖርም ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፬/፲፱፻፺፮ (እንደተሻሻለ) እና ደንቡን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች መሠረት የተፈቀዱ ማበረታቻዎች ተፈጻሚነት ይቀጥላል።

፪/ ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፬/፲፱፻፺፮ (እንደተሻሻለ) እና ደንቡን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለተፈቀዱ ማበረታቻዎች ብቁ ሆኖ በመብቱ ያልተጠቀመ ባለሀብት በዚህ ደንብ መሠረት በሚፈቀዱ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ለመሆን ከመረጠ ይህንን አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት በማስታወቅ የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ይችላል።

15. Transfer of Duty-Free Imported Goods

1/ Capital goods or construction materials or motor vehicles imported free of customs duty may be transferred to persons with similar duty-free privileges.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, the capital goods or construction materials or motor vehicles imported free of customs duty may be transferred, upon effecting payment of the appropriate customs duty, to persons having no similar duty-free privileges.

3/ The investor may re-export the duty-free imported capital goods or construction materials or motor vehicles.

4/ Any investor who contravenes the provisions of this Article shall be punishable in accordance with the relevant provisions of the Customs Proclamation.

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

16. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation No.84/2003 (as amended) is hereby repealed.

2/ No regulation, directive or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters provided for in this Regulation.

17. Transitory Provisions

1/ Notwithstanding the provision of Article 16 of this Regulation, incentives granted pursuant to the Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation No. 84/2003 (as amended) and the directives issued there under shall continue to be effective.

2/ Where an investor eligible for incentives granted pursuant to the Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation No.84/2003 (as amended) and directives issued there under has not yet exercised his right, opts instead to be a beneficiary of incentives provided for in this Regulation, he may notify the appropriate investment organ and be entitled thereto.

፲፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፳ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

18. Effective Date.

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 29th day of November, 2012.

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## ሠንጠረዥ

## የኢንቨስትመንት መስኮች እና የገቢ ግብር ማበረታቻዎች

| ተ.ቁ. | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| ፩ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ | | |
| | ፩.፩ የምግብ ኢንዱስትሪ | | |
| | ፩.፩.፩ ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን ማቀነባበር<br>፩.፩.፪ ዓሣና የዓሣ ውጤቶችን ማቀነባበር<br>፩.፩.፫ ፍራፍሬ እና/ወይም አትክልት ማቀነባበር<br>፩.፩.፬ የምግብ ዘይት ማምረት<br>፩.፩.፭ ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ውጤቶችን ማምረት<br>፩.፩.፮ ስታርች እና የስታርች ውጤቶችን ማምረት<br>፩.፩.፯ ዱቄት ማምረትን ሳይጨምር ጥራጥሬ፣ የቅባት እህል ወይም ሌላ እህል ማቀነባበር<br>፩.፩.፰ ሌሎች ምግቦችን ማምረት | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፩.፱ ስኳር ማምረት | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፮ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፩.፲ ቸኮሌት፣ ከረሜላ፣ ብስኩት ወይም ሌሎች ጣፋጭ ምግቦችን (አይስክሬም እና ኬክን ሳይጨምር) ማምረት | ለ፩ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፩.፲፩ ማካሮኒ፣ ፓስታ እና/ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

## SCHEDULE

## INVESTMENT AREAS AND INCOME TAX EXEMPTIONS

| No. | Investment Areas | In Addis Ababa and Special Zone of Oromia surrounding Addis Ababa | In Other Areas |
|---|---|---|---|
| 1 | **Manufacturing** | | |
| | 1.1 **Food Industry** | | |
| | 1.1.1 Processing of meat and meat products<br>1.1.2 Processing of fish and fish products<br>1.1.3 Processing of fruit and/or vegetables<br>1.1.4 Manufacture of edible oil<br>1.1.5 Processing of milk and/or manufacture of dairy products<br>1.1.6 Manufacture of starches and starch products<br>1.1.7 Processing of pulses, oil seeds or cereals, excluding flour production<br>1.1.8 Manufacture of other food products | Exemption from income tax for 3 years | Exemption from income tax for 5 years |
| | 1.1.9 Manufacture of sugar | Exemption from income tax for 5 years | Exemption from income tax for 6 years |
| | 1.1.10 Manufacture of chocolate, candy, biscuits and other sweets (excluding ice crème and cakes) | Exemption from income tax for 1 year | Exemption from income tax for 2 years |
| | 1.1.11 Manufacture of macaroni, pasta and/or similar products | Exemption from income tax for 3 years | Exemption from income tax for 5 years |

| ተ.ቁ. | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | ፩.፩.፲፪ የሕጻናት ምግብና ወተት፣ ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ፣ እርሾ ፣ ሆምጣጤ ፣ ማዮኔዝ ፣ ሰው ሰራሽ ማር፣ አዮዲን የተጨመረበት ጨው ወይም መሰል ምግቦችን ማምረት<br>፩.፩.፲፫ የእንስሳት መኖ ማቀነባበር | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፪ የመጠጥ ኢንዱስትሪ | | |
| | ፩.፪.፩ የአልኮል መጠጥ ማምረት | ለ፩ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፪.፪ የወይን ጠጅ ማምረት | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፪.፫ ቢራ እና/ወይም የቢራ ብቅል ማምረት | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፪.፬ ለስላሳ መጠጥ፣ የማዕድን ወይም የታሸጉ ሌሎች ውሃዎችን ማምረት | ለ፩ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፫ የጨርቃጨርቅና የስፌት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| | ፩.፫.፩ የጥጥ፣ የሱፍ፣ የሐር እና የመሳሰሉ የጨርቃጨርቅ ጭረቶችን ማዘጋጀትና መፍተል | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፫.፪ ጨርቃጨርቅ መሸመን፣ ማጠናቀቅና ማተም | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፮ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፫.፫ ጣቃ ጨርቅ፣ ክር፣ ድርና ማግ፣ አልባሳትና ሌሎች የጨርቃጨርቅ ውጤቶችን በማንጣት፣ በማቅለም፣ በማኮማተር፣ በማፍካት፣ በማጠንከር፣ ወርድንና ቁመትን በመጠበቅ ወይም በማስዋብ ማጠናቀቅ | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፫.፬ ሌሎች የጨርቃጨርቅ ማጠናቀቅ ሥራዎች | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| No. | Investment Areas | In Addis Ababa and Special Zone of Oromia surrounding Addis Ababa | In Other Areas |
|---|---|---|---|
| | 1.1.12 Manufacture of baby food, roasted and ground coffee, soluble coffee, tea, yeast, vinegar, mayonnaise, artificial honey, iodized salt or similar food products<br>1.1.13 Processing of animal feeds | Exemption from income tax for 2 years | Exemption from income tax for 4 years |
| | 1.2 **Beverage Industry** | | |
| | 1.2.1 Manufacture of alcoholic beverages | Exemption from income tax for 1 year | Exemption from income tax for 2 years |
| | 1.2.2 Manufacture of wine | Exemption from income tax for 3 years | Exemption from income tax for 4 years |
| | 1.2.3 Manufacture of beer and/or beer malt | Exemption from income tax for 2 years | Exemption from income tax for 3 years |
| | 1.2.4 Manufacture of soft drink, mineral water or other bottled water | Exemption from income tax for 1 year | Exemption from income tax for 2 years |
| | 1.3 **Textile and Textile Products Industry** | | |
| | 1.3.1 Preparation and spinning of cotton, wool, silk and similar textile fibers | Exemption from income tax for 4 years | Exemption from income tax for 5 years |
| | 1.3.2 Weaving, finishing and printing of textiles | Exemption from income tax for 5 years | Exemption from income tax for 6 years |
| | 1.3.3 Finishing of fabrics, yarn, warp and weft, apparel and other textile products by bleaching dyeing, shrinking, sanforizing, mercerizing or dressing | Exemption from income tax for 3 years | Exemption from income tax for 4 years |
| | 1.3.4 Other textile finishing activities | Exemption from income tax for 2 years | Exemption from income tax for 3 years |

| ተ.ቁ. | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | ፩.፫.፭ ሹራብ ወይም ፎጣ ማምረት<br>፩.፫.፮ ከአልባሳት በስተቀር የተዘጋጁ ጨርቃጨርቆችን ማምረት<br>፩.፫.፯ ምንጣፍ ማምረት | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፫.፰ የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትን (የስፖርት አልባሳትን ጨምሮ) ማምረት<br>፩.፫.፱ የጨርቃጨርቅ ውጤቶች ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፮ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፬ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| | ፩.፬.፩ ባለቀለት ደረጃ ቆዳና ሌጦ ማልፋት | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፮ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፬.፪ ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | ፩.፬.፫ የቆዳ ውጤቶችን (ሻንጣ፣ቦርሳ፣የቆዳ ኳስ እና የመሳሰሉትን) ማምረት<br>፩.፬.፬ የቆዳ ጫማ ማምረት<br>፩.፬.፭ የቆዳ ውጤቶች ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፮ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፭ የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| | የእንጨት ውጤቶችን (እንጨት መሰንጠቅን፣ ጣውላ ማምረትን እና ቀድመው የተዘጋጁ የእንጨት ውጤቶችን መገጣጠምን ሳይጨምር) ማምረት | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፮ የወረቀት እና የወረቀት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| | ፩.፮.፩ ፐልፕ ማምረት<br>፩.፮.፪ ወረቀት ማምረት | ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፮ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፮.፫ የወረቀት ማሸጊያዎችን ማምረት | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| No. | Investment Areas | In Addis Ababa and Special Zone of Oromia surrounding Addis Ababa | In Other Areas |
|---|---|---|---|
| | 1.3.5 Manufacture of knitted and crocheted fabrics<br>1.3,6 Manufacture of made-up textile articles, except apparel<br>1.3.7 Manufacture of carpets | Exemption from income tax for 4 years | Exemption from income tax for 5 years |
| | 1.3.8 Manufacture of wearing apparel (including sport wears)<br>1.3.9 Manufacture of accessories for textile products | Exemption from income tax for 5 years | Exemption from income tax for 6 years |
| | 1.4 **Leather and Leather Products Industry** | | |
| | 1.4.1 Tanning of hides and skins up to finished level | Exemption from income tax for 5 years | Exemption from income tax for 6 years |
| | 1.4.2 Tanning of hides and skins below finished level | Not eligible for income tax exemption | Not eligible for income tax exemption |
| | 1.4.3 Manufacture of leather products (luggage, hand bags, leather balls and similar products)<br>1.4.4 Manufacture of leather shoe<br>1.4.5 Manufacture of accessories for leather products | Exemption from income tax for 5 years | Exemption from income tax for 6 years |
| | 1.5 **Wood Products Industry**<br>Manufacture of wood products (excluding saw milling timber making and assembling of semi-finished wood products) | Exemption from income tax for 2 years | Exemption from income tax for 3 years |
| | 1.6 **Paper and Paper Products Industry** | | |
| | 1.6.1 Manufacture of pulp<br>1.6.2 Manufacture of paper | Exemption from income tax for 5 years | Exemption from income tax for 6 years |
| | 1.6.3 Manufacture of paper packages | Exemption from income tax for 3 years | Exemption from income tax for 4 years |

| ተ.ቁ. | የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|---|
| | ፩.፭.፬ ሌሎች የወረቀት ውጤቶችን ማምረት | ለ፩ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፮ የማተሚያ ኢንዱስትሪ | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| | ፩.፯ የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| | ፩.፯.፩ መሠረታዊ ኬሚካሎችን (ኢታኖልን ጨምሮ) ማምረት<br>፩.፯.፪ ማዳበሪያ እና/ወይም የናይትሮጅን ውህዶችን ማምረት | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፮ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፯.፫ የፕላስቲክ እና/ወይም የሰው ሠራሽ ጎማ ጥሬ ዕቃዎችን ማምረት<br>፩.፯.፬ ፀረ-ተባይ፣ ፀረ-አረም ወይም ፀረ-ሻጋታ ማምረት | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፯.፭ የማድማዳ ቀለም፣ ቫርኒሽ ወይም መሰል መለሰኛዎችን፣ የማተሚያ፣ የመጻፊያ ወይም የሥዕል ቀለም ወይም ማጣበቂያ ማምረት<br>፩.፯.፮ ሳሙናና ዲተርጀንት፣ ማፅጃና መወልወያ፣ ሽቶ እና መሰል መዋቢያዎችን ማምረት | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፯.፯ ሰው ሠራሽ ጭረቶችን ማምረት | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፮ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፯.፰ ሌሎች የኬሚካል ውጤቶችን (ባሩድ፣ ፊንጂ፣ የፎቶግራፍ ፊልም እና የመሳሰሉትን) ማምረት | ለ፪ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፰ የመሠረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ዝግጅት ኢንዱስትሪ | | |
| | ፩.፰.፩ ለመድኃኒት ግብዓትነት የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃኒት ውጤቶችን ማምረትና ማዘጋጀት | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፮ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| | ፩.፰.፪ መድኃኒት ማምረት ወይም ማዘጋጀት | ለ፫ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ፬ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

